ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

*የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ*
*ህዳር 14 ቀን 2008 ዓ.ም. የተላለፈ*

# የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም !

ኢትዮጵያዊ ሆኖ ሰብዕናውን እያስከበረ ሀገሩን ለማዳን እስካሁን ያልተሳካለት ቡድንና ስብስብ ሁሉ ፤ አሁንም ከባዕዳን ጥገኝነት ነፃ ሊወጣ አልቻለም ። ነፃ ለመውጣትም ፈቃደኝነቱን አላሳየም ። ጭራሽ አይፈልግምም ! የሀረግ-እሬሳ ተፈጥሮና ባኅርይ ያለው ሁሉ፤ ከጥገኝነት ራሱን ነፃ ያወጣል ተብሎም የሚጠበቅ አይደለም ። ይህ በበኩሉ ፤ ባዕዳን በሀገራችን ጉዳይ ጣልቃ እየገቡ የራሳቸውን ፖሊሲ እንዲፈፅሙ በር ከፍቶላቸዋል ። እግረ መንገዳቸውንም ፤ ኢትዮጵያ የእነርሱ ጥገኛ ሀገር ሆና እንድትቀር አድርጓታል ። ይህ እስከመቸ ይቀጥላል ?

መልሱን ለሚመለከተው ሁሉ እንተወዋለን ። ዕውነታውን ግን፤ ማንም ሊክደው አይችልም ። ይኸም በበኩሉ ፤ ሀገራችን ፤ ባለቤት የሌላት ሀገር ሆና ትታያለች ። ዛሬ ! አብዛኛው ነው ማለት ባይቻልም፤ በማንነት ፍለጋ ላይ የሚንከራተተው የኅብረተሰብ ክፍል ፤ ሁነኛ የሆነ የአገር- አድን መፍተሄ ለማግኘት አልቻለም ። "የጨነቀው ሙቅ አነቀው " ነውና አሁንም፤ የኢትዮጵያን ችግር ባዕዳን ይፈቱታል የሚለው አስተሳሰብ ስር እየሰደደ በመሄድ ላይ ይገኛል ። ይህም በበኩሉ ኢትዮጵያዊው ሁሉ በአንድ ላይ በመተባበር ለሀገሩ መፍትሄ ራሱ እንዳይፈልግ ትልቅ ደንቃራ ሆኖ ቆይቷል ። የአዲሱ ቅኝ ግዛት ተገዥነት ሥነ ልቦና ቀስ በቀስ ሳይታወቅ ሥራውን እየሰራ ነው ማለት ሳይቻል ይቀራል ?

ይኸ በመሆኑም ፤ ለአለፉት በርካታ ዓመታት የተደረገው ጥረት ሁሉ፤ በአመዛኙ የተጠበቀውን ውጤት ማስመዘገብ አልቻለም ። እስካሁን ድረስ፤ የአንድነት ኃይሉ ፤ ሲባክን የቆየው፤ <u>በማንነት</u> ፍለጋ ላይ በመተረማመስ ላይ ነበር ማለት ይቻላል። ያ ማ ባይሆን ኖሮ ፤ በአሁኑ ወቅት፤ ሁነኛ ውጤትን ሊያመጣ የሚችል፤ አስተማማኝ ተግባር ማስመዘገበ በተቻለ ነበር ።

ለዚህ ሁኔታ ግን ፤ አንዱ ወቃሽ ሌላው ተወቃሽ ሊሆን አይችልም። ከብደቱና ስፋቱ ይለያይ እንደሁ እንጅ ፤ ሁሉም ተጠያቂነትና ኃላፊነት አለበት። ይህንን ሀቅ አምኖ መቀበል ከተቻለ ፤ ምናልባት ሁሉም በአንድነት ወደ አንድ አቅጣጫ ሊያተኩር ወደሚያስችል ጉዞ ሊራመድ ይችላል ተብሎ ይገመታል ።

ይህ እንዲመጣ ከተፈለገ ደግሞ ፤ ሁሉም ራሱን ይጠይቅ ! ጓዳውን ይፈትሽ ! አመለካከቱን ይመርምር ! ጣት መጠቋቆሙ እስካሁን የትም አላደረሰ ። አንዱ በሌላው ላይ ጣት መቀሳሰሩ አንዱን አቸናፊ ሌላው ተቸናፊ ሊያደርገው አልቻለም። አቸናፊና ተቸናፊ በሌለበት ሁኔታ፤ የሁሉንም ውድቀት

ያስከትላል። አወዳደቁ ደግሞ የአህያ ውድቆሽ ሆኖ ይቀራል ። ይኽ የግርግር ውድቀት በሚፈጥረው ሁኔታ ፤ ተጠቃሚ የሆኑት ግን ወያኔና ባዕዳን መሆናቸውን መገንዘብ አለብን ! እነርሱ በእኛ እየቀለዱ ፤ እኛም በእነርሱ እየተሽማቀቅን መቀጠል የለብንም ። አይገባንም ። በቃ ብለን እንድንነሳ፤ ሁኔታው አስገዳጅ ከሆነ ቆይቷል ። ቆራጥ ርምጃ ልንወስድ የሚገባን ጊዜው ካለፈ ውሎ-አድሯል ። ያልጠረጠረ እንደሚመነጠር ሁሉ ፤ ያልቆረጠም እንደተልፈሰፈሰ ይቀራል እንጅ ፤ ቅስመ- ሰባራ ከመሆን አይድንም ። ቅስምን እየሰበሩ ደግሞ ውጤት ለያስመዘግብ የሚችል ትግል ማካሄድ አይቻልም ። የሕዝብን ቅስም ሰባሪ የሆነውን ጠላት ፤ ማስወገድ ይዋል ይደር የሚባል ሥራ አይደለም።

" **ዘጠኝ ዲፕሎማዎች አንድ ዲግሪ ሊሆኑ** " እንደማይችሉ ሁሉ፤ የመድረክ ጫጫታ፤ የስብሰባ ጋጋታ፤ የሰልፍ ዳንኪራ ፤ የፓልቶክ ድንፋታ ፤ የመግለጫ አቤቱታ፤ ብቻውን ያመረቃ ውጤት እስካሁን ሊያስመዘግብልን አልተቻለውም ። ሰሚ ያጣ ጩኸት ፤ ምንጊዜም፤ የገደል ማሚቶ ከመሆን አይልፍም ።

ሰልፉ ውይይቱና የጋራ ወሳኔዎች እንዲሁም፤ መግለጫውና አቤቱታው፤ ሁሉ መቀጠል እንደሚገባቸው እንደጠጠበቀ ሆኖ ፤ ወያኔን የሚያስወግድ ኃይልና ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ፤ ሁኔታዎች ሊለወጡ አይችሉም። **የመላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ አመፅ ያካተተ የአንድነት ኃይል ትግል ነው የመጨረሻው አቸናፊ የሚሆነው** ። ባዕዳኑንም፤ የሚያሰጋና የሚያስደነግጥ ይህ ሀገራዊ ጠቅላላ ሕዝባዊ አመፅ ለመሆኑ፤ ዋቢ አምጡ የሚባልበት አይደለም።

ያ ኃይል እስካልተፈጠረ ድረስ ፤የኢትዮጵያ ሁኔታ እንዲህ እንደተንጠለጠለ ይቆያል። የተቃዋሚዎች የትግል ስልት ፤ መሰረታዊ የይዘት ለውጥ እስካላደረገ ደረስ ፤ የትግልን ዕመርታ ማየት አይቻልም ። ይህንን ሁኔታ በደንብ አለመንገንዘብ ፤ የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በትክክል አለመገምገም ብቻ ሳይሆን ፤ የጠላትን ኃይል አሰላለፍ በሚገባ አለመረዳትም ጭምር ይሆናል ። የጠላትንና የወዳጅን ኃይል አሰላለፍ በትክክል መረዳት ደግሞ የትግል አልፋ-ዖሜጋ ብቻ ሳይሆን ፤ ወደ ድል ጎዳና የሚያመራ ወሳኝ ሚና ሊያጫውት የሚያስችል ዘዴ መሆኑ ፤ በተመክሮ የተፈተነ ሀቅ ነው ።

የተገኘውን አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም ፤ ባዕዳኑ በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ እንዲገቡ ምክንያት ከሆነው አንዱ፤ የእኛ የራሳችን ድክመትና አለመተባበር ለመሆኑ ማነኛችንም አሌ ልንለው አንችልም ። እርስ በእርሳችን ሳንተዋወቅ በመናናቅና በመፈራራት ስለተለያየን ለመቀራረብ ተቸግርናል ። ቀድመን ሳንተዋወቅ በምናደርገው መፈረጃጀት የተነሳ፤ ማጠፊያው ከሚቸግረን ጣጣ ውስጥ እንገባለን ። "ማወቅ መውደድ ነው እንዲሉ፤ ካለመተዋወቅ የተነሳ ፤ መግባባት አልተቻለም ። መግባባት ከሌለ ደግሞ መተባበር አይመጣም ። ይልቁንም ፤ ለመጠራጠርና ላለመተማመን፤ ብሎም፤ ለሀሜታና አሉባልታ በር ይከፍታል ።

**<u>የዚህ ሁሉ ምክንያት ፤ ዓላማን ለሕዝብ ተገዥነት ላይ የተመሠረተ ዕምነት</u> አለመኖሩ ነው ።** ከሁሉ አስቀድሞ ፤ ለሕዝብ ተገዥነት ላይ የተመሠረተ ዕምነት እንዲኖር ያስፈልጋል ። የማነኛውም ትግል ፤ መሠረቱ የሕዝብ ሉዓላዊነት እስከሆን ድረስ፤ የመጨረሻው አቸናፊ የሚሆነውም ፤ ያው ራሱ ሕዝቡ መሆኑን አምኖ መቀበል ግዴታ ነው ። በዚህ መሠረታዊ ዕምነት ላይ ስምምነት ካለ፤ በሕዝብ አቸናፊነት ዙሪያ ተሰባስቦ መተባበር ፤ ለነገ -ተነገ

ወዲያ የሚያስተላልፉትና በቀነ- ቀጠሮ ፋይል የሚያስቀምጡት ጉዳይ አይደለም ። እስከዛሬ ደረስ ፤ እያረረ የሚስቀውን ጥርሱን እንጅ፤ እየደማ የሚያለቅሰውን የሕዝቡን ልብ አላውቅነውም ። አልተረዳነውም ። ህመሙን ፤ ሰቆቃውንና ጉዳቱን በሚገባ አላወቅንለትም ። ለዚህም እኮ ነው ሕዝቡ፤

**"ሳርር እስቃለሁ እንደ ማሽላ ፤**

***ህዘን ከሆዴ እየተብላላ !"***

እያለ የመከራ ኑሮውን የሚገፋው ! ሕዝቡን ፤ ጥርሱን እንጅ፤ ሀዘንተኛውን ልቡን ልናይለት አልቻልንም ። በየስበባውና በየሰልፉ የሚገለጸው ጭብጨባና ፉጨት የድጋፍና የደስታ መግለጫ ብቻ እንደሆነ በመቆጠር፤ በሆዱ ያለውን ሀዘንና እሮሮ በአንክሮ እንዳናይለት አድርጎናል ። ይህም፤ ከተሳሳተ እይታ ላይ በመውደቅ፤ አቅጣጫ ቢስ ወደ ሆነ ማእዘን እንድናተኩር ተገድደናል ። የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ደግሞ ፤ የአንድነት ኃይሉ ፤ እንዳይሰባሰብ ምክንያት ሆኗል ። ተሰባስበው አንድነት ካላመጡ ደግሞ፤ ትርፉ፤ ተበታትኖ መቅረት ብቻ ነው። ይኸንን ደግሞ ጠላቶቻችን አጥብቀው ይፈልጉታል ።

ሁኔታውን ለመለውጥና ከሀገር ጥቅም አንጻር ለምቆጣጠር መደረግ ያለባቸውን ስናይ፤

1ኛ. የኢትዮጵያ አንድነት ኃይል ፤ ባስቸኳይ በመሰባሰብ የኅብረት ኃይል ፈጥሮ መንቀሳቀስ አለበት ። ነገር ከተበላሸ በኋላ ፤ ግርግር መፍጠርና የተቃውሞ መግለጫዎች ለማውጣት መሽቀዳደሙ ፋይዳ አያመጣም ። ከሎንዶኑ ጉባዔ በኋላ የነበረውን ዋይታና ለቅሶ ያጤኗል ። " እኛማ ፤ አስቀድመን ተናግረን ነበር " የሚል ምጸት ማሰማት ባንሻም ፤ ሊሆን የሚችለውን አስቀድመን መጠቆሙ ግን ግዴታችን እንደሆነ እንቆጥረዋለን ።

2ኛ. የአንድነት ኃይሉ ተጠናክሮ መውጣት ማለት ፤ የሀገሪቱን የወደፊት ፤ ዕድል ለመወሰን በሚደረገው ማንኛውም ሁኔታ፤ መንገድና ስብሰባ ሁሉ፤ ወሳኝ ሚና ለመጫወት የሚችል ኢትዮጵያዊ ኃይል ተፈጠረ ማለት ነው ። በመሆኑም ፤ የሀገሪቱን የፖለቲካ መልከዐ- ምድር የኃይል ሚዛን በእጅጉ ያጠነክረዋል። የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ባሰተማማኝ ደረጃ ለማስከበር የሚችል ሀገራዊ ኃይል ተፈጠረ ማለት ነው ። ይህንን ኢትዮጵያዊ ኃይል፤ መላው የሀገሪቱ ሕዝብ ከዳር እስከዳር እንደሚደግፈው፤ እንደሚተባበረውና ሙሉ ፈቃዱን እንደሚለግሰው መጠራጠር አይቻልም ።

3ኛ. ለዚህ ሀገራዊ ኃይል በስቸኳይ መፈጠር የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ወቅታዊና አንገብጋቢ ጥያቄ መሆኑን አምኖ፤ የአንድነት ኃይሉ በአስቸኳይ ተሰባስቦ ሀገራዊ ኅብረት እንዲፈጥር የኢትዮጵያን መኖር የሚፈልግ ዜጋ ሁሉ ፤ የመጀመሪያው ጥሪ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል ።

" ጌታዋን የተማመነች በግ፤ ላቷን ውጭ ታሳድር ይሆናል " " የአህያ ባል ግን ከጅብ አያስጥልም። "በመሆኑም፤ የሀገራችን ጠላቶች፤ የማታ ማታ ፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣ፤ ጌቶቻቸው አያስጥሏቸውም !

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !